በአ¥‰ B¼¤‰êE KL§êE mNGoT
ፍትህ ቢሮ
የሕግ ምክር፣ማርቀቅና ማጠቃለል ዳይሬክቶሬት

THE AMAHARA NATIONAL REGIONAL STATE
JUSTICE BUREAU
LEGAL COUNSELING, DRAFTING AND COMPILATION
DIRECTORATE

ቁጥር የሕ/ም/ማጠ/ዳ/ 3087/18

ቀን 02/06/2018 ዓ.ም

ለአብክመ ግብርና ቢሮ
ባህር ዳር፤

ጉዳዩ፦ የመመሪያ ምዝገባን ይመለከታል

በአማራ ክልል የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 292/2017 ዓ.ም እንደተደነገገው ማንኛውም የአስተዳደር ተቋም አዲስ መመሪያ አውጥቶ ተግባራዊ ከማድረጉ በፊት መመሪያውን ከነማብራሪያው እንዲሁም አዋጅ ከመውጣቱ በፊት በሥራ ላይ የነበሩ መመሪያዎችን አዋጁ በወጣ በ1 (አንድ) ዓመት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ለፍትህ ቢሮው በመላክ እንዲመዘገብ ማድረግ እንዳለበት ተደንግጓል።

በዚህ መሰረት የአብክመ ግብርና ቢሮዉ በቁጥር ግቢ/ርኃ/112/19 በቀን 15/05/2018 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ "የግብርና ኤክስቴንሽን አደረጃጀት እና የድጋፍና ክትትል መመሪያ ቁጥር ሰኔ /2016" የሚባል መመሪያ እንዲመዘገብ መላኩ ይታወሳል።

ስለሆነም ፍትህ ቢሮ በአዋጁ አንቀጽ 16 መሠረት የተላከለትን መመሪያ ሕጋዊነቱን፣ መሰረታዊ መብቶችና መርሆችን የማይጥስ መሆኑን መርምሮ መመሪያው በክልል ደረጃ መመሪያ ቁጥር 44/2018 ዓ.ም ሆኖ ስራ ላይ እንዲዉል የመዘገበው ስለሆነ የተመዘገበውን መመሪያ 15 ገጽ በሀርድና ሶፍት ኮፒ በዚህ ሽኚ ደብዳቤ አባሪ በማድረግ የላክን መሆኑን እንገልጻለን።

'ከሰላምታ ጋር'

ሺድጋፍ ኃይሌ
የክልል ዐቃቤ ሕግ

ግልባጭ//

- ለቢሮ ኃላፊ ጽሕፈት ቤት፤ (ያለ አባሪ)
- ለፍት/ሕግ ጉዳ/ዘር/ምክትል ቢሮ ኃላፊ ጽሕፈት ቤት
  ፍትሕ ቢሮ

# መመሪያ ቁጥር 44/2018

## የግብርና ኤክስቴንሽን አደረጃጀት እና የድጋፍና ክትትል መመሪያ

በሃገራችን የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት መስጠት ከተጀመረ ከ50 በላይ አመታትን ያስቆጠረ ሲሆን በርካታ የኤክስቴንሽን ስርዓቶችም ተግባራዊ ሲደረጉ ቆይተዋል፡፡ በመሆኑም በሀገር አቀፍ ደረጃ ከ2002 ዓ/ም ጀምሮ ተግባራዊ እየተደረገ በሚገኘው የተሳትፎዓዊ የግብርና ኤክስቴንሽን ስርዓት ስር የአደረጃጀት እና የድጋፍና ክትትል መመሪያ ተዘጋጅቶ ግብርናና ገጠርን ማዕከል ያደረገ የልማት ፖሊሲና ስትራተጂ ተቀይሶ ሲተገበር የቆየ ሲሆን በተቀየሰው የአሰራር መመሪያ የአርሶ አደሮች የልማት ቡድን እና የ1ለ5 አደረጃጀት በተለይም የህዝብ ንቅናቄ በሚፈልጉ ስራዎች ላይ የነበረው አስተዋጾ ቀላል የሚባል ባይሆንም በመደበኛ የስርጸት ስራችን ላይ ግን በሚፈለገው ደረጃ ውጤት ማስመዝገብ ያልቻለ ሲሆን በተለይም ባለፉት 10 አመታት አደረጃጀቱ ዉጤታማ ባልመሆኑ አሁን ካለው የግብርና ፖሊሲና ስትራቴጅ ጋር ማጣጣም አስፈልጓል፡፡

በመሆኑም ላለፉት ዓመታት በስራ ላይ የቆየው የግብርና የኤክስቴንሽን አደረጃጀት እና የድጋና ክትትል መመሪያ ለግብርና ቴክኖሎጂ ስርጸት የሚጠበቀዉን ያህል አስተዋጽኦ አለማድረጉ፣ ለግብርና ተልዕኮ ሙሉ በሙሉ ትኩረት አለመስጠቱ፣ ከጊዜ ወደ ጊዜ የኤክስቴንሽን ተጠቃሚ ቁጥር እየጨመረ በመምጣቱና መልዕክቶችን በፍጥነት ወደ ሁሉም አርሶአደሮች ለማድረስ አስቸጋሪ እየሆነ በመምጣቱ፣ ጊዜውን የሚዋጅ አደረጃጀት በማስፈለጉ፣ ከባህላዊ አስተራረስ ወደ መካናይዜሽን ፣ ኮመርሽያላይዜሽን ፣ ክላስተራይዜሽን እና በአዲስ የተቀረጸውን የብዙ ተዋንያን የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት ውጤታማ በማድረግ የእውቀትና የቴክኖሎጂ ሽግግሩን ማፋጠን አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የአማራ ብሐራዊ ክልላዊ መንግስት ግብርና ቢሮ በተሻሻለዉ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት አስፈፃሚ አካላት እንደገና ማቋቋሚያና ሥልጣንና ተግባራት መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 300/2017 ዓ.ም አንቀፅ 19 ንዑስ አንቀፅ (1) (ሰ) ድንጋጌ ስር በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

# ክፍል አንድ

# ጠቅላላ ድንጋጌዎች

## 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የግብርና ኤክስቴንሽን አደረጃጀት እና የድጋፍና ክትትል መመሪያ ቁጥር 44/2018 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 2. ትርጓሜ

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፦

1/ **"አርሶ አደር"** ማለት መደበኛ ወይም ቋሚ መተዳደሪያው የግብርና ሥራ የሆነ ማንኛውም ሰው ነው፡፡

2/ **"የአርሶ አደር ማሠልጠኛ ማዕከል"** ማለት በአንድ የገጠርም ሆነ የከተማ ቀበሌ አስተዳደር ውስጥ የተቋቋመ ሆኖ ለአርሶ አደሮች የንድፈ ሀሳብና የተግባር ሥልጠና የሚሰጥበት፣ የተሻሻለ የግብርና ቴክኖሎጂና አሠራርን ለማስተዋወቅና ለማስረፅ፣ የትምህርት፣ የሥልጠና እና የመረጃ አገልግሎት ለመስጠት የሚያገለግል ነው፤

3/ **"የገጠር ቀበሌ አስተዳደር"** ማለት በክልሉ የሚገኝ የታችኛው አስተዳደር እርከን ነው፡፡

4/ **"ቀጠና"** ማለት በአንድ ቀበሌ ውስጥ እንደ ቀበሌው የቆዳ ስፋት እና የህዝብ ብዛት የግብርናን ስራ በቀላሉ ለማስተባበር በሚያመች መንገድ የሚከፋፈሉ ንዑሳን የቀበሌ አካላት ናቸው፡፡

5/ **"የቀጠና የግብርና ተጠሪ"** ማለት በቀጠና ደረጃ ከ5-7 የግብርና ልማት ቡድኖችን በማቀፍ የግብርና ልማት ስራን ለማስተባበር እና በቀበሌ ባለሙያዎች እና በግብርና ልማት ቡድን መካከል እንደ ድልድይ ሆኖ የሚያገለግል ሲሆን በአንድ ቀበሌ የሚኖረው የቀጠና የግብርና ተጠሪ እንደቀበሌው የህዝብ እና የግብርና ልማት ቡድን ብዛት ይወሰናል፡፡

6/ **"የግብርና ልማት ቡድን"** ማለት ቁጥራቸው ከ25-35 የሚደርሱ አባወራ እና እማወራ አርሶአደሮችን በመንደራቸው በማደራጀት ስለ ግብርና እና ሌሎች ተያያዥ የልማት ስራቸው እየተወያዩ የሚመሩበት አደረጃጀት ነው፡፡

7/ **"ንዑስ የግብርና ልማት ቡድን/ የስራ ቡድን/"** ማለት ግብርና ል/ቡድኑ ውስጥ ያሉ መስራት የሚችሉ የቤተሰብ አባላት በሙሉ የሚደራጁበትና 3ቱ የግ/ል/ቡድኑ



የአብክመ ፍትሕ ቢሮ * The ANRS Bureau of Justice * የህግ ምክር፣ ማርቀቅና ማጠቃለያ ዳይሬክቶሬት

አመራሮች ተከፋፍለው የሚያስተባሩት ነው፡፡

8/ "የቀበሌ ግብርና ልማት ባለሙያ/ሰራተኛ" ማለት በቀበሌ ደረጃ ተመድቦ የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት የሚሰጥ የእንስሳት ሀብት ልማት ፣ የሰብል ልማት ፣ የተፈጥሮ ሀብት ፣ የመስኖ ፣ የእንስሳት ህክምና ፣ የእንስሳት አዳቃይ ቴክኒሽያን ፣ የኅብረት ስራ ማኅበር ባለሙያን የሚያካትት ነው፡፡

9/ "የቀበሌ ግብርና ልማት ጽ/ቤት ኃላፊ" ማለት በቀበሌ ደረጃ የግብርና ልማት ባለሙያዎችን የሚያስተባብር፣ የሚደግፍ፣ የሚከታተልና የሚቆጣጠር ማለት ነው፡፡

10/ "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

11/ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው ሁሉ ሴትንም ይጨምራል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የቀበሌ የግብርና ኤክስቴንሽን አደረጃጀት

### 3. የቀበሌ የግብርና ኤክስቴንሽን አደረጃጀት

1/ ማንኛውም የቀበሌ የግብርና ኤክስቴንሽን አደረጃጀት በሚከተሉት መርሆዎች ላይ የተመሰረተ መሆን አለበት፤

ሀ) ፈቃደኝነት

ለ) አሳታፊነት

ሐ) አካታችነት

መ) ተደራሽነት

ሠ) ከወገንተኝነት የጸዳ

ረ) ተጠያቂነት

2/ በቀበሌ ደረጃ የሚኖሩ የግብርና ኤክስቴንሽን አደረጃጀቶች የሚከተሉት ናቸዉ፡፡

ሀ) የግብርና የቀጠና ተጠሪ፣

ለ) የግብርና ልማት ቡድን፣

ሐ) ንዑስ የግብርና ል/ቡድን (የስራ ቡድን)፣

መ) በግብርና ልማት ስራ የተደራጁና የሚደራጁ የወጣት ኢንተርፕራይዝ ቡድኖች ናቸዉ፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተገለጹት አደረጃጀቶች መንደርን መሰረት በማድረግ ለአመታዊ እና ቋሚ የግብርና ልማት አገልግሎቶች የሚያገለግል ይሆናሉ፡፡

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተገለጹት አደረጃጀቶች እንደተጠበቀ ሆኖ ማሳን እና የሚመረቱ ምርቶችን ተመሳሳይነት መሰረት በማድረግ የሚከተሉት አደረጃጀቶች

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፍትሕ ቢሮ The ANRS Bureau of Justice የህግ ምክር ማጠናቀቅ

ይኖራሉ፡፡

ሀ) የማሳ ኩታ ገጠም ዲጋፊ /ACC/ አደረጃጀት (የክላስተሩ አባላት ቁጥር እና መሪዎች እንደየ ኮሞዲቲው የሚወሰን ይሆናል)

ለ) የአ/አደሮች ምርት ክላስተር /FPC/ አደረጃጀት (የክላስተሩ አባላት ቁጥር እና መሪዎች እንደየ ኮሞዲቲው የሚወሰን ይሆናል)

ሐ) የአ/አደሮች የመስክ ትምህርት ቤት /FFS/ የክላስተሩ አባላት ቁጥር እና መሪዎች እንደየ ኮሞዲቲው የሚወሰን ይሆናል)

መ) ሌሎች በግብርና ልማት ስራ ወሳኝ አስተዋጾ አላቸው ተብሎ በመመሪያ የተላለፉና በቀጣይም የሚተላለፉ አደረጃጀቶችም ውጤታማነታቸው እየተገመገመ በስራ ላይ የሚውሉ ይሆናል፡፡

## 4. የግብርና ልማት የቀጠና አደረጃጀት

በአንድ ቀበሌ የሚኖረው የግብርና የቀጠና ተጠሪ ብዛት በቀበሌው የአባወራ/እማወራ እንዲሁም የልማት ቡድን ቁጥር የሚወሰን ሆኖ አንድ ቀጠና ከ5-7 የግብርና የልማት ቡድኖች እንዲያቅፍ ተደርጎ ይደራጃል፡፡

1/ እስከ 750 አባወራና እማወራ ባሉበት ሶስት የቀጠና አስተባባሪዎች፤

2/ ከ750-1000 አባወራና እማወራ ባሉበት አምስት የቀጠና አስተባባሪዎች፤

3/ ከ1000-1500 አባወራና እማወራ ባሉበት ስድስት የቀጠና አስተባባሪዎች፤

4/ ከ1500 አባወራና እማወራ በላይ ስምንት የቀጠና አስተባባሪዎች ይኖሩታል፡፡

## 5. የግብርና የቀጠና ተጠሪ የመመልመያ መስፈርት

የግብርና ልማት የቀጠና ተጠሪ ከአርሶ አደሮች መካከል የሚመረጥ ሆኖ ተጠሪነቱም ለቀበሌው ግብርና ልማት ጽ/ቤት ይሆናል፤

1/ ገበያ ተኮር በሆኑ የግብርና ምርቶች ላይ ትኩረት አድርጎ የሚያመርት፣

2/ የግብርና ስራውን ቢዝነስ ፕላን አዘጋጅቶ በተገቢው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት የሚተገብር፣

3/ ለአካባቢው የተቀመጠውን የምርታማነት ግብ በማረጋገጥ ገቢውን ያሳደገ፣

4/ ተገቢውን የእርሻ መረጃ መዝገቦ የሚይዝ፣

5/ ለሌሎች አርሶ አደሮች በማሳየት እና በመደገፍ አርአያ የሆነ፣

6/ ማንበብ እና መጻፍ የሚችል፤

7/ የወሰደውን የግብርና ግብዓት ብድር ወቅቱን ጠብቆ የሚከፍል፤

8/ በሌሎች ተደራራቢ የኮሚቴ ስራዎች ያልተጠመደ፤

## 6. የግብርና የቀጠና ተጠሪ ተግባርና ኃላፊነት

የግብርና የቀጠና ተጠሪ የሚከተለው ተግባርና ኃላፊነት ይኖረዋል፤

1/ በቀበሌ ግብርና ባለሙያዎችና በግብርና ልማት ቡድን መካከል ትስስር እና የመረጃ ልውውጥን ማሳለጥ፤

2/ ቀጠናውን ወክሎ በሚካሄድ የግብርና ልማት ስብሰባዎች መሳተፍ፤

3/ የቀጠናው የግብርና ልማት ቡድን መሪዎች እና አባላቶች ፍላጎት መሰረት ለስልጠና ማነሳሳትና ማስተባበር፣

4/ ተቀባይነት ያገኙ የግብርና ቴክኖሎጂዎች እና ምርጥ ተሞክሮዎችን በመጠቀም አርአያ መሆንና በቀጠናው የሚገኙ ቡድን አባላት በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸውና እንዲሳተፉ ማነሳሳትና ማስተባበር፡፡

## 7. የግብርና የቀጠና ተጠሪዎች የግንኙነት ሁኔታ

1/ በየ15 ቀኑ ከቀበሌ ግብርና ጽ/ቤት ጋር ምክክር ካሂዳሉ፤

2/ በስራቸው ከሚገኙ የግብርና ልማት ቡድን መሪዎች፣ የሴት የልማት ህብረት የግብርና ተጠሪ እና በግብርና ልማት ስራ በኢንተርፕራይዝ ከተደራጁ የወጣት አስተባባሪዎች ጋርም በየ15 ቀኑ ይወያያሉ፤

3/ በስራቸው ከሚገኙ የግብርና ልማት ሁሉም አባላት ጋር በወር አንድ ጊዜ ይወያያሉ፤

4/ እንደአስፈላጊነቱ አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠሩ ይችላል፡፡

## 8. የግብርና ልማት ቡድን አወቃቀርና አመራሮች

1/ አንድ የግብርና ልማት ቡድን ከ25 እስከ 35 አባላት ይኖሩታል፣

2/ የግብርና ልማት ቡድኑ አመራሮችም ሰብሳቢ፣ ም/ሰብሳቢ እና ጸሐፊ እንዲኖረው ሆኖ የሚደራጅ ሲሆን ቢያንስ ከአመራር አባላት አንዷ ሴት ብትሆን ይመረጣል፤

3/ በግብርና ልማት ቡድኑ ሶስቱ አመራሮች በስራቸው የሚያስተባብሩት ሶስት የስራ ቡድን (ንዑስ ልማት ቡድን) እንዲኖራቸው ተደርጎ ይደራጃሉ፡፡

4/ የንዑስ ልማት ቡድን (የስራ ቡድን) አደረጃጀትና አሰራር

ሀ) አንድ የቤተሰብ አባላት ሆነው እድሜአቸው ከ15-64 ዓመት የሆኑና መስራት የሚችሉትን ያካተተ ሆኖ ይደራጃል፤

ለ) ንዑስ ልማት ቡድን 1 ( የስራ ቡድን 1)፣ ንዑስ ልማት ቡድን 2 ( የስራ ቡድን 2) ንዑስ ልማት ቡድን 3 ( የስራ ቡድን 3) ብሎ መሰየም /ማደራጀት ይቻላል፡፡

ሐ) ይህ አደረጃጀት ዋና ስራው የተ/ሃብት ልማት ስራ ቢሆንም ሌሎች ተጨማሪ የአካባቢ የልማት ስራዎች ላይም (የቀበሌ ግብርና ተቋማት ግንባታና ጥገና ፣ መንገድ ስራና ጥገና ፣ የመስኖ ቦይ



The ANRS Bureau of Justice የህግ ምርምር ማጠናቀር

ጠረጋ ፣ አደገኛና መጤ አረሞችን ማስወገድ ---) ላይ እንዲሳተፍ ይደረጋል።

## 9. የግብርና ልማት ቡድን መሪ መመልመያ መስፈርቶችና ተግባርና ኃላፊነት

1/ የግብርና ልማት ቡድን መሪ መመልመያ መስፈርቶች የሚከተሉት ናቸዉ።

ሀ) ማንበብ እና መጻፍ የሚችል፤

ለ) ለአካባቢው የተቀመጠውን የምርታማነት ግብ ያረጋገጠ፣

ሐ) አርሶ አደሮች በማሳየት እና በመደገፍ አርአያ የሆነ፣

መ) የወሰደውን ብድር ወቅቱን ጠብቆ ክፍያውን የሚፈጽም፤

ሠ) ተገቢውን የእርሻ መረጃ መዝግቦ የሚይዝ፣

ረ) ቢዝነስ ፕላን የማዘጋጀት ልምድ ያዳበረ፤

ሰ) በሌሎች ተደራራቢ የኮሚቴ ስራዎች ያልተጠመደ፤

2/ የግብርና ልማት ቡድን መሪ ተግባርና ኃላፊነት የሚከተሉት ናቸዉ።

ሀ) ከቀጠና አስተባባሪና ከቀበሌ ግብርና ባለሙያዎች ጋር በግብርና ልማት ቡድን መካከል ትስስር እና የመረጃ ልውውጥን ማሳለጥ፤

ለ) ቡድኑን ወክሎ የግብርና ልማት ስብሰባዎች መሳተፍ፤ በቡድን ደረጃ ለሚካሄዱ ስብሰባዎች የውይይት አጀንዳ መቅረጽ፤ ስብሰባ መምራት፤

ሐ) የቡድኑን አባላት ፍላጎት መሰረት አድርጎ ለስልጠና ማነሳሳት፣

መ) ተቀባይነት ያገኙ የግብርና ቴክኖሎጂዎች እና ምርጥ ተሞክሮዎችን በመጠቀም አርአያ መሆንና በቡድኑ የሚገኙ አባላት በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸውና እንዲሳተፉ ማነሳሳትና ማስተባበር፤

ሠ) የእርስ በእርስ የተግባር መማማር የሚካሄድባቸው መድረኮች በወር አንድ ጊዜ ያስተባብራል፤

ረ) የልማት ቡድን አመራሮች የተግባር ድልድል ያደርጋል፤ ተግባራቸውን በአግባቡ መወጣታቸውን ይከታተላል፤ሪፖርት ያጠናክራል፤

ሰ) እንዲመራ የተሰጠውን የስራ ቡድን ያስተባብራል፤

ሸ) ከቀጠናው ተጠሪ እና ከቀበሌ ባለሙያ የሚሰጡ ተጨማሪ ተግባራት ተቀብሎ ያስፈጽማል።

3/ የግብርና ልማት ቡድን ምክትል ሰብሳቢ ተግባርና ኃላፊነት የሚከተሉት ናቸዉ።

ሀ) የቡድኑ ሰብሳቢ በማይኖርበት ወቅት ተክቶ ቡድኑን ያስተባብራል፤

ለ) ተቀባይነት ያገኙ የግብርና ቴክኖሎጂዎች እና ምርጥ ተሞክሮዎችን በመጠቀም አርአያ መሆን

ሐ) በስሩ ያለውን የስራ ቡድን ያስተባብራል፤

መ) ከቡድን መሪው/ሰብሳቢ/ እና ከቀበሌ ባለሙያ የሚሰጡ ተጨማሪ ተግባራት ተቀብሎ ያስፈጽማል፡፡

4/ የፀሐፊው ተግባርና ኃላፊነት የሚከተሉት ናቸዉ፡፡

ሀ) ሰብሳቢው እና ም/ሰብሳቢው በማይኖሩበት ወቅት ቡድኑን ያስተባብራል፤

ለ) የአባላትን ሙሉ መረጃ፣ ከግብርና ልማት ቡድኑ የተሰበሰቡ መሰረታዊ መረጃዎችን፤ የውይይት ቃለጉባዔዎችን ያዘጋጃል፤ ሲፈለግም ሰብሳቢውን አሳውቆ ለተጠቃሚ ይሰጣል፤

ሐ) በስሩ ያለውን የስራ ቡድን ያስተባብራል፤

መ) ከሰብሳቢ/፣ ምክትል ሰብሳቢው እና ከቀበሌ ባለሙያ የሚሰጡ ተጨማሪ ተግባራት ተቀብሎ ያስፈጽማል፡፡

## 10. የግብርና ልማት ቡድኖች ግንኙነትና ወርሃዊ የተግባር መማማር አፈጻጸም

1/ በቋሚነት በሳምንት አንድ ጊዜ አማካይ በሆነ ቦታ ላይ ተገናኝተው በወቅታዊ የግብርና ልማት ተግባራት ዙሪያ ምክክር የሚያደርጉ ሲሆን እንደስራ ወቅታዊነት ደግሞ የድርጊት መረሃ-ግብሩን መሰረት በማድረግ ምክክር ያደርጋሉ፡፡

2/ አስቸኳይ ጉዳዮች ሲያጋጥሙ ቋሚ የመገናኛ ጊዜውን ሳይጠብቁ ይገናኛሉ ፣ አዳዲስ መረጃዎችን ፣ መልዕክቶችን እና ሪፖርቶችን በተለያዩ አማራጮች መረጃ ይለዋወጣሉ፡፡

3/ በወር አንድ ቀን በቡድኑ ውስጥ በሁሉም የግብርና ልማት ዘርፎች በተሰሩ እና እየተሰሩ ባሉ የተሻሻሉና አስተማሪ ተግባራት ዙሪያ የተግባር መማማር ያደርጋሉ፡፡

4/ ዋናው የተግባር መማማሪያ በል/ቡድኑ ውስጥ የተለየው የተሻሻለ አሰራር እና ቴክኖሎጅ ቢሆንም ከግብርና ል/ቡድኑ ውጭም እንደቀጠና እና ቀበሌ ሄዶ ልምድ መቅሰም ያለባቸው ሲሆን ቢያንስ በ3 ወር አንድ ጊዜ በሌሎች የግብርና የልማት ቡድኖች የተሰሩ አስተማሪ ተሞክሮዎችና ልምዶች መለዋወጫ ቢሆን ጥሩ ነው፡፡

5/ ለመማማሪያነት የሚመረጠው ተግባር አስተማሪነቱ በቀበሌ ባለሙያዎች መረጋገጥ ያለበት ሆኖ የሚመረጠው ተግባር የግድ የቴክኖሎጅ ውጤት ብቻ ላይሆን ይችላል (አ/አደሩ በራሱ እውቀት የሰራቸው አስተማሪ ተግባራት ፣ የአፈር ለምነት ማሻሻያ ፣ የደን አግሮፎረስትሪ ፣ የእ/እርባታ ፣ የሰብልና ፍራፍሬ ሙሉ ፓኬጅ ወዘተ-----) ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

6/ በመማማር ሂደቱ ዉስጥ ውጤቱን ብቻ ሳይሆን ከጅምሩ የአሰራር ሂደቱን ጭምር እያወቁት እንዲሄዱ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

7/ የቀበሌ ባለሙያዎች በአንድ የግብርና ልማት ቡድን ውስጥ ቢያንስ በሁሉም ሙያዎች አስተማሪ እና ሞዴል ስራዎች እንዲኖሩ አቅደዉና አልመው መስራት ይኖርባቸዋል፡፡

8/ የተግባር መማማር ሂደቱ ደርሶ የመመለስ እና በጣም አሰልቺም እንዳይሆን በጥንቃቄ መምራት የሚያስፈልግ ሲሆን (የተሻሻለው አሰራር ከመተግበሩ በፊት የነበረውን ሁኔታ ፣ ተግባሩን በማከናወን ሂደት የነበሩ ሁኔታዎችና ፣ ከተከናወነ በኃላ የመጣውን ውጤት ) የተግባሩ ባለቤት ከገለጸ በኃላ የቡድኑ አባላት (ምን እንደተማሩ ፣ ያልገባቸው ካለ እና በቀጣይ ወደራሳቸው ወስደው ለማስፋት በሚያስችሉ ጉዳዮች ዙሪያ መግባባት ያስፈልጋል፡፡)

9/ የመማማር ሂደቱ እንደ ወረዳ በተዘጋጀ እና ወጥ በሆነ መዝገብ ላይ በየቀኑ እየተመዘገበ መያዝ ይኖርበታል፡፡

## 11. የሴቶች አደረጃጀትና ድጋፍ አሰጣጥ

1/ በክልሉ ሴቶች የማደራት ስልጣን የተሰጠው በየደረጃው ላለ የሴቶች ህጻናትና ማህበራዊ ጉዳይ ተቋም ቢሆንም የተደራጀውን የሴቶች ቡድን እንደየ ሴክተሮች የስራ ባህሪ እያጣጣሙ ሴቶች የልማቱ ተሳታፊ ብቻ ሳይሆን ተጠቃሚ እንዲሆኑም ጭምር አልሞ መስራት ይጠይቃል፡፡

2/ በሳምንት አንድ ቀን በሚካሄደው የግብርና ልማት ቡድን ውይይት የሴቶች የልማት ህብረት የግብርና ልማት ተጠሪዋ በመገኘት ተልዕኮ ተወስዳለች ፣ ትሰጣለች እንዲሁም ተግባራዊነቱንም ትከታተላለች፡፡

3/ በወር አንድ ጊዜ በግብርና ልማት ቡድኑ ውስጥ በሚካሄደው የተግባር መማማር የሴቶች የልማት ህብረት የግብርና ተጠሪዋ ተገኝታ ልምድ እንድትወስድና ለሌሎች አባላቶቿ ልምዱን እንድታካፍል ይደረጋል፡፡

4/ ሴቶቹን በአደረጃጀታቸው እቅድየመስጠት፣ የመገምገም፣ ስልጠናዎችን የመስጠት፣ በልምድ ልውውጦች የማሳተፍ፣ በንቅናቄ የማሳተፍ እና ሌሎች ተጨማሪ ተግባራት ላይ ማሳተፍ ሲፈለግ በሴቶች የልማት ህብረት የግብርና ልማት ተጠሪዋ አማካኝነት ጥሪ በማስተላለፍ መደገፍ የሚቻል ሲሆን በወር አንድ ጊዜ በቋሚነት ሙሉ አባላቱን በመያዝ የግብርና ባለሙያዎች እንዲደግፉ ይደረጋል፡፡

5/ የቀበሌ ግብርና ባለሙያዎች እና የቀጠና የግብርና ልማት ተጠሪው ሴቶቹን በተለያዩ አጀንዳዎች በአካል ተገኝቶ ማወያየት ሲፈልግ የሴቶች ልማት ህብረት የግብርና ልማት ተጠሪዋን ፕሮግራም እንድትይዝ በማድረግ ያወያያል፡፡

## 12. ለወጣቶች ስለሚሰጥ የሙያ ድጋፍ

1/ በተናጥልም ይሁን በቡድን በግብርና ልማት ሙያ ዘርፍ ለተሰማሩና በቀጣይም ለሚሰማሩ

ወጣቶች በቀበሌ ግብርና ባለሙዎች የሙያ ድጋፍ ይደረግላቸዋል፡፡

2/ በግብርና ስራ የሚተዳደሩ በወጣት እድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ወጣቶች የዋናው የግብርና ልማት ቡድን አካል በመሆን ይደራጃሉ፡፡

3/ በግብርና የሙያ ዘርፍ የስራ እድል የሚፈጠርባቸውን ጸጋዎችን በመለየት ወጣቶቹ የስራ እድል እንዲፈጠርላቸው በየደረጃዉ ከሚገኙ የስራና ስልጠና ተቋማት ጋር በመቀናጀት ይሰራል፡፡

## ክፍል ሦስት

## ስለ ድጋፍ፣ ክትትልና ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 13. በየደረጃው የሚዋቀር የቴክኒክ ቡድን

1/ ከክልል አስከ ወረዳ ያለ በየደረጃው የሚዋቀረው የቴክኒክ ቡድን የግብርና ኤክስቴንሽን ዘርፍ የሚያስተባብረውና እንደ ወቅቱና የአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ የሚወሰን ሆኖ በዋናነት፡-

ሀ) የግብርና ኤክስቴንሽን ባለሙያ----አስተባባሪ

ለ) የእንስሳት ሃ/ልማት ባለሙያ---------አባል

ሐ) የሰብል ልማትና ጥበቃ ባለሙያ-------አባል

መ) የተፈጥሮ ሃ/ል/ጥበቃ ባለሙያ--------አባል

ሠ) የአት/ፍራ/መ/ውሃ አጠቃቀም ባለሙያ---አባል

ረ) የምግብ እና ስነ-ምግብ ባለሙያ -----አባል

ሰ) የሥርዓተ ጾታ ባለሙያ---------አባል የሆኑበት የቴክኒክ ባለሙያዎች ቡድን

የሚደራጅ ሲሆን እንደአስፈላጊነቱ የሚጨመር እና የሚቀነስ ይሆናል፡፡

2/ በየደረጃው ያሉ የቴክኒክ ቡድኖች በተዋረድ ባላቸዉ መዋቅር ተገኝተው ድጋፍ የሚሰጡ ሲሆን የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከላትን መጎብኘት እና በቀበሌ ጽ/ቤት ደረጃ ውይይት ማካሄድ ትኩረት የሚሰጠዉ ሆኖ አፈጻጸሙም እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

**ሀ) በክልል ደረጃ**

- ✓ የክልል የቴክኒክ ቡድን ክልሉን በአመች ቀጠናዎች በመከፋፈል ቢያንስ በሩብ ዓመት አንድ ጊዜ ለዞኖች የሙያ ድጋፍ መስጠት ይኖርበታል፡፡
- ✓ በዞን ሁለት ወረዳዎች እና ከየወረዳው ሁለት ቀበሌዎችን መደገፍ ይኖርበታል፡፡

**በአንድ ቀበሌ ደግሞ፡-**

- ✓ 1 የግብርና የቀጠና ተጠሪ እና በስሩ ያሉ 2 የግብርና ልማት ቡድኖችን እና ከ 3-5



The ANRS Bureau of Justice

ሌሎች አርሶ አ/ደሮችን የስራ እንቅስቃሴ እና ወርሃዊ የተግባር መማማር ሂደት ይደግፋል።

- ✓ 2 የሴቶች የልማት ህብረት ቡድኖችን እና በስሩ ያሉ ከ2-3 ሌሎች ሴቶችን
- ✓ 1 በግብርና ልማት የተደራጁ የወጣቶች ቡድን (ኢንተርፕራይዝ) እና በስሩ ያሉ ከ2-3 ወጣቶችን
- ✓ 2 የማሳ ኩታ ገጠም ደጋፊ አረጃጀቶችን እና በስሩ ያሉ ከ2-3 አባላትን
- ✓ የአርሶ አደሮች ማሰልጠኛ ማዕከላትን ፣ ተፋሰሶችን እና ችግኝ ጣቢያዎችንም የድጋፍ አሰጣጡ አካል ማድረግ ይገባል።

ለ) **በዞን ደረጃ**

- ✓ የዞን የቴክኒክ ቡድን ቢያንስ በ2ወር አንድ ጊዜ ለወረዳዎች የሙያ ድጋፍ ይሰጣል፤
- ✓ የዞን የቴክኒክ ቡድን በዞኑ ስር ያሉትን ወረዳዎች ከ2-3 ቡድን በመከፋፈል ሁሉንም ወረዳዎች መደገፍ የሚገባ ሲሆን ከእያንዳንዱ ወረዳ 2 ቀበሌዎችን መደገፍ ይኖርበታል።

**በአንድ ቀበሌ ደግሞ፡-**

- ✓ 1 የግብርና የቀጠና ተጠሪ እና በስሩ ያሉ 2 የግብርና ልማት ቡድኖችን እና ከ 3-5 ሌሎች አርሶ አ/ደሮችን የስራ እንቅስቃሴ እና ወርሃዊ የተግባር መማማር ሂደት ይደግፋል።
- ✓ 2 የሴቶች የልማት ህብረት ቡድኖችን እና በስሩ ያሉ ከ2-3 ሌሎች ሴቶችን
- ✓ 1 በግብርና ልማት የተደራጁ የወጣቶች ቡድን (ኢንተርፕራይዝ) እና በስሩ ያሉ ከ2-3 ወጣቶችን
- ✓ 2 የማሳ ኩታ ገጠም ደጋፊ አረጃጀቶችን እና በስሩ ያሉ ከ2-3 አባላትን
- ✓ የአርሶ አደሮች ማሰልጠኛ ማዕከላትን ፣ ተፋሰሶችን እና ችግኝ ጣቢያዎችንም የድጋፍ አሰጣጡ አካል ማድረግ ይገባል።

ሐ) **በወረዳ ደረጃ**

- ✓ የወረዳ የቴክኒክ ቡድን ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ ቀበሌዎችን ይደግፋል፤
- ✓ የወረዳ የቴክኒክ ቡድንን ቢያንስ ከ2-3 ቡድን በመከፋፈል እያንዳንዱ ቡድን በወረዳው ውስጥ ያሉትን ቀበሌዎች 50% በአንደኛው ዙር እና ቀሪ ቀበሌዎችን ደግሞ በ2ኛው ዙር ይደግፋል፥ ከተቻለ ግን ሁሉንም ቀበሌዎች በአንድ ዙር ቢደግፍ ይመረጣል፤

**በአንድ ቀበሌ ደግሞ፡-**

- ✓ 2 የግብርና የቀጠና ተጠሪ እና በስሩ ያሉ 2 የግብርና ልማት ቡድኖችን እና ከ 5-7 ሌሎች አርሶ አ/ደሮችን የስራ እንቅስቃሴ እና ወርሃዊ የተግባር መማማር ሂደት ይደግፋል።
- ✓ 2 የሴቶች የልማት ህብረት ቡድኖችን እና በስሩ ያሉ ከ2-3 ሌሎች ሴቶችን
- ✓ 1 በግብርና ልማት የተደራጁ የወጣቶች ቡድን (ኢንተርፕራይዝ) እና በስሩ ያሉ ከ3-5 ወጣቶችን

- ✓ 2 የማሳ ኩታ ገጠም ደጋፊ አረጃጀቶችን እና በስሩ ያሉ ከ5-7 አባላትን
- ✓ የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከላትን ፣ ተፋሰሶችን እና ችግኝ ጣቢያዎችንም የድጋፉ አካል ማድረግ ይገባል፡፡

በአጠቃላይ የቴክኒክ ቡድኑ ድጋፍ ትኩረት የሚያደርገው በየደረጃው ያሉ የእውቀት እና የክህሎት ክፍተቶችን በመለየት፣ በመሙላትን በመደጋገፍ ላይ የተመሰረተ ሆኖ በዋናነት በየአካባቢው የተገኙ ምርጥ ተሞክሮዎችን በመለየትና በመቀመር ወደ ሌሎች አካባቢዎች የማስፋት ተግባራትን ታሳቢ ያደረገ መሆን ይኖርበታል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ በየደረጃዉ በሪፖርት የተላለፉ መረጃዎች መሬት ላይ ስለመኖራቸዉ የተለያዩ ስልቶችን ነድፎ መደገፍና መከታተልም የሚገባ ይሆናል፡፡

3/ በቀበሌ የግብርና ልማት ባለሙያ የሚሰጥ የሙያ ድጋፍ የቀበሌ የግብርና ልማት ባለሙያዎች የስራ ስምሪት 75% የግል ሙያቸውን እና 25% ደግሞ በጋራ ስራዎች ላይ መሰረት በማድረግና ሳምንታዊ የስራ ፕሮግራም በማውጣት በቀበሌ ግብርና ጽ/ቤት ኃላፊው አማካኝነት በማጸደቅ እንደሚከተለዉ ይተገበራል፤

**ሀ) የቀበሌ ግብርና ልማት ባለሙያዎች/ሰራተኞች ሳምንታዊ የስራ ፕሮግራም በሳምንት አምስት (5) ቀን የመስክ ድጋፍ የሚያደርግ ሲሆን በየቀኑ፡-**

- ✓ 2 የቀጠና የግብርና ተጠሪዎችን እና ከእያንዳንዳቸው 1 የግብርና ልማት ቡድን እና ከ3-5 ሌሎች አባላትን ይጎበኛል፤
- ✓ 1 የሴቶች የልማት ህብረት መሪ እና በስሩ ቢያንስ ከ2-3 ሌሎች ሴችን ይጎበኛል፤
- ✓ 1 በግብርና ልማት የተደራጀ የወጣቶች ቡድን (ኢንተርፕራይዝ) እና ከ1-2 ወጣት ይጎበኛል፤
- ✓ 3 የማሳ ኩታ ገጠም ደጋፊ አረጃጀቶችን እና በስሩ ያሉ ከ7-10 ሌሎች የክላስተሩ አባላትን
- ✓ የአርሶ አደሮች ማሰልጠኛ ማዕከላትን ፣ ተፋሰሶችን እና ችግኝ ጣቢያዎችንም የድጋፉ አካል ማድረግ ይገባል፡፡
- ✓ አንድ ቀን የሳምንታዊ ሪፖርት ማጠናቀሪያ እና አንድ ቀን ደግሞ ሳምንታዊ የእረፍት ቀን ሲሆኑ የእረፍት ቀናትን አስመልክቶ የቀበሌዉን ነባራዊ ሁኔታ መሰረት በማድረግ ባለሙያዎቹ ከቀበሌዉ ጽ/ቤት ኃላፊ ጋር በመሆን በሚያወጡት ፕሮግራም መሰረት የሚተገበር ሆኖ የቀበሌ ጽ/ቤቱ ለአገልግሎት ክፍት ሆኖ በወረፋ እንዲያርፉ መደረግ አለበት፡፡

ለ) የቀበሌ ግብርና ኃላፊ ሳምንታዊ የስራ ፕሮግራም

- ✓ በሳምንት ሶስት ቀን የመስክ ድጋፍና ባለሙያዎቹ በመስክ ያላቸውን እንቅስቃሴ በተግባር የሚያረጋግጥ ሲሆን በሳምንት ውስጥ ቢያንስ (2 የቀጠና የግብርና ተጠሪዎችን ፣ 5 የግብርና ልማት ቡድን፣ 3 የሴቶች የልማት ህብረት መሪ፣ 1 በግብርና ልማት የተደራጀ የወጣቶች ቡድን (ኢንተርፕራይዝ) ፣ 3 የማሳ ኩታ ገጠም ደጋፊ አረጃጀቶችን እና ከነዚህ አደረጃጀቶች ከ10-15 አባላትን በአካል መደገፍ ያለበት ሲሆን ቢያንስ 50% ሴቶች መሆን አለባቸው፡፡
- ✓ ሌሎች ቀሪ ቀናቶችን በማጣጣም ለቀበሌ ባለሙዎች ሳምንታ የስራ ፕሮግራ ማውጣት፣ ቼክሊስት ማዘጋጀት፣ ግ/መልስ መስጠት ፣ ከቀበሌ አመራሮች እና ሌሎች ኮሚቴዎች ጋር በግብርና ልማት ስራው ዙሪያ ውይይቶችን ማካሄድ፣ ሪፖርቶችን አጠቃሎ

ለሚመለከተው መላ እና ሌሎችን ተግባራት መሰረት በማድረግ በቀበሌው ማዕከል ሆኖ የሚያስተባር ይሆናል፡፡

**4/ የቀበሌ ግብርና ልማት ባለሙያዎች ተጠሪነት**

- ✓ የቀበሌ ግብርና ልማት ባለሙያዎች ተጠሪነታቸው ለቀበሌው ግብርና ጽ/ቤት ኃላፊ ይሆናል፡፡
- ✓ የቀበሌው ግብርና ጽ/ቤት ኃላፊ ተጠሪነት 2006 በወጣው የቀበሌ ጽ/ቤት ማቋቋሚያ መመሪያ ላይ አንቀጽ 6 ላይ ተጠሪነታቸው ለወረዳው ግብርና ጽ/ቤት እንዲሆን የተወሰነ ቢሆንም በተደጋጋሚ ያጋጠመውን ችግር መሰረት በማድረግ ቢሮው በ22/11/2013 ተጠሪነታቸው በውክልና ለግብርና ኤክስቴንሽን ኮሙኑኬሽን ቡድን እንዲሆን የወሰነ በመሆኑ ቀጣይም በሌላ መመሪያ እስካልተሻረ ድረስ በዚሁ መንገድ የሚፈጸም ሆኖ ማንኛውም የመንግስት፣ የፕሮጀክት፣ የፕሮግራም እና ሌሎች የግል ተቋማትም ጭምር የቀበሌ ግብርና ባለሙያዎችን ከምድብ ስራቸው ውጭ ለሆነ ማንኛውም ተጓዳኝ ስራም ይሁን የተለያዩ ስብሰባና ስልጠናዎች ሲፈልጓቸው የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት ስራውን የማይጎዳ ስለመሆኑ ለግብርና ኤክስቴንሽን ዘርፍ ቀርቦና በተቋሙ ኃላፊ ይሁንታ ተሰጥቶበት ብቻ የሚፈጸም ይሆናል ፡፡

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 14. መመሪያን ከሌሎች ሰነዶች ጋር አጣጥሞ ስለመስራት

ይህ መመሪያ በሀገር አቀፍ ደረጃ ከሚዘጋጁ የግብርና ኤክስቴንሽን ፖሊሲ፣ ስትራቴጅዎች እና አዋጆች ጋር ተጣጣሞ ተግባራዊ ይሆናል፤

### 15. ስለተፈቀዱና የተከለከሉ ተግባራት

1/ ማንኛውም የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት አቅራቢ በቀበሌ ደረጃ የተደራጁ የቀጠናና የግብርና ልማት ቡድንን ከመጠቀም አይከለከልም፤ ነገር ግን ከቀበሌው ግብርና ጽ/ቤት ጋር መረጃ በመለዋወጥ ተፈጻሚ ይሆናል፤

2/ ማንኛዉም የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት አቅራቢ በቀጠናና በግብርና ልማት ቡድን አደረጃጀት ስራውን መተግበር እንደተጠበቀ ሆኖ እንደሚያቀርበው የአገልግሎት ዓይነትና እንደተጠቃሚው ፍላጎት ከወሰደው ስምምነት ሳይወጣ የራሱን የአደረጃጀት ስልት ነድፎ ስራውን ከማከናወን አይከለከልም፤

3/ የተደራጀውን የቀጠና የግብርና ልማት ተጠሪ እና የግብርና ልማት ቡድን ለሌላ የፖለቲካ አላማ መጠቀም አይቻልም ፡፡

4/ ማንኛውም የልማት ተቋም በቀበሌ ደረጃ የተደራጁ የቀጠናና የግብርና ልማት ቡድንን ከመጠቀም አይከለከልም፤ ነገር ግን ከቀበሌው ግብርና ጽ/ቤት ጋር መረጃ በመለዋወጥ ተፈጻሚ ይሆናል፤

5/ ማንኛውም የመንግስት፣ የፕሮጀክት፣ የፕሮግራም እና ሌሎች የግል ተቋማትም ጭምር የቀበሌ ግብርና ባለሙያዎችን ከምድብ ስራቸው ውጭ ለሆነ ማንኛውም ተጓዳኝ ስራም ይሁን የተለያዩ ስብሰባና ስልጠናዎች ሲፈልጓቸው የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት ስራውን የማይጎዳ ስለመሆኑ ለግብርና ኤክስቴንሽን ዘርፍ ቀርቦና በተቋሙ ኃላፊ ይሁንታ ተሰጥቶበት የሚፈጸም ይሆናል ።

## 16. ስለ ተሻሩና ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸዉ ሕጎች

1/ ከዚህ በፊት በስራ ላይ የዋሉት የመደበኛ አደረጃጀት መመሪያዎች በዚህ መመሪያ ተሽረዋል።

2/ ይህን መመሪያ የሚቃረን ማናቸውም ሌላ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ መመሪያ ውስጥ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

## 17. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

1/ ይህ መመሪያ ከሃምሌ 1/2016 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል።

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ይህ መመሪያ እንደገና አዲስ ቁጥር ከተሰጠበት ቀን በኋላ ያለ መብት ወይም ግዴታ ሕጋዊ ውጤት የሚኖረው መመሪያው በአማራ ክልል ፍትህ ቢሮ ተመዝግቦ በግብርና ቢሮ ድረ-ገጽ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ ይሆናል።

**ድረስ ሳህሉ(ዶ/ር)**

**በም/ር/መ/ማ/የገጠር**

**ልማት ክላስተር አስተባባሪ እና**

**የግብርና ቢሮ ኃላፊ**

ሰንጠረዥ 1: በቀበሌ ደረጃ በተለያዩ ኮሚቴዎች የተወከለ የህብረተሰብ ቁጥር አሰላል ታሳቢዎች በአማካይ 1200 አባወራ በሚኖርበት አንድ ቀበሌ የሚኖር ኮሚቴ ታሳቢ.

| ተ/ቁ | የኮሚቴው አይነት | ብዛት | ታሳቢዎች |
|---|---|---|---|
| 1 | የእማወራ እና አባወራ ልማት ቡድንና 1ለ5 መሪዎች | 240 | 1200/25 *5=240 |
| 2 | የሴቶች ልማት ቡድንና 1ለ5 መሪዎች | 240 | 1200/25 *5=240 |
| 3 | የወጣቶች ልማት ቡድንና 1ለ5 መሪዎች | 80 | |
| 4 | የማሳ ኩታ ገጠም ደጋፊ አደረጃጀት መሪዎች | 160 | |
| 5 | የንዑስ ተፋሰስ ኮሚቴዎች | 55 | 5*11=55 |
| 6 | የደን ግብረሃይል | 7 | |
| 7 | የተባይ መከላከል ግብረሃይል | 6 | |
| 8 | የእንስሳት በሽታ ቅኝት ኮሚቴ | 7 | |
| 9 | የቅድሚያ ማስጠንቀቂያና ምላሽ ኮሚቴ | 7 | |
| 10 | የመስኖ ውሃ ኮሚቴ | 7 | |
| 11 | የአካባቢ ጥበቃና መሬት አስተዳደር ኮሚቴ | 9 | |
| 12 | የገበሬ ማሰልጠኛ ኮሚቴ | 4 | |
| 13 | የጤና፣ የትምህርት፣ የጸጥታ፣ የሴቶች ወዘተ... | --- | |
| | | 822 | 70% የኮሚቴ አባል ወይም ከ1 በላይ የያዙ በጣም ብዙ ናቸው። |

ዕዝል 2: የአወቃቀር ሰንሰለት ከክልል እስከ አ/አደር

